


# የአስሩ ልጃገረዶች ምሳሌ

- አንድ ቀን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለአንድ የሰርግ ድግስ ታሪክ ተናገረ። ስለዚህ ሰርግ ታሪክ ከመስማታችን በፊት በመጀመሪያ የአይሁድን የሰርግ ወግ እንመልከት።

- የአይሁድ ሠርግ በረጅም ጊዜ የሚፈፀሙ ሶስት ደረጃዎች አሉት። ተጋቢዎች በወጣትነት እደሜያቸው ነው ወላጆቻቸው ለጋብቻ ሁኔታዎችን የሚያመቻቹላቸው። የትዳር ጓደኛ መረጣ የሚካሄደውም በወላጆች ነው። አንዳንዴ ይህ የሚፈፀመው በሌሎች የተጋቢዎቹን አቻነት በመወሰን ከሚረዱ ሰዎች ጋር ነው። ይህ የመጀመሪያው ደረጃ ነው።

- ሁለተኛው ደረጃ ደግሞ በሙሽራይቱ ቤት የሚካሄድ የመተጫጨት ሥርዓት ነው። በዚሁ ጊዜም ተጋቢዎቹ ቃል ይገባባሉ። ወንዱ ሙሽራም ለሴቷ ሙሽራ ስጦታዎችን ያበረክታል። ይህ ስርዓት አንድ አመት ተኩል ገደማ የሚፈጅ ስርዓት ነው። ሆኖም ሙሽራይቱ አሁንም የምትኖረው ከቤተሰቦቿ ጋር ነው። ታዲያ በዚህ ወቅት ሙሽራይቱ ለሙሽራዋ እንደታጨች ይታሰባል።

- ከዚህ ቀጥሎ የእራት ሳምንት ተብሎ የሚታወቀው ስርዓት ይመጣል። ብዙውን ጊዜ የሚፈፀመው ምሽት ላይ ነበር። ሙሽራውና ጓደኞቹ ወደሙሽራይቱ ቤት ይመጣሉ። ሙሽራይቱ ወፍራም የፊት መሸፈኛ ታደርጋለች። ሙሽራይቱና ጓደኞቿም ሙሽራውን አጅበውት ወደ ሙሽራው አባት ቤት ወይንም ሰፋ ወዳለና የሠርጉ ስነሥርዓት ወደሚፈፀምበት አዳራሽ ይሄዳሉ። ፈርማም ይፈራረማሉ። ከፊርማው በኋላም ሙሽራና ሙሽሪት አብረው ጊዜ ያሳልፋሉ። ከዚያም ሙሽራው ከሙሽሪት ጋር ለሰባት ቀናት አብሯት ይቆያል።

በሳምንቱ መጨረሻም ፊቷን የሸፈነችበትን ወፍራም መሸፈኛ ታነሳና የሰርጉ ታዳሚዎች ወደተሰበሰቡበት ቦታ ትመጣለች። ከዚያም ሁሉም ሰው ፊቷን ያየዋል። ይህ በሶስተኛ ደረጃ የሚፈፀመው ሥርዓት ልጃገረዲቱ ፊፅማ ያላገባች ከሆነ በሰባት ቀናት ውስጥ ባሏ ሞቶባት ለሁለተኛ ጊዜ የምታገባ ሴት ከሆነች ደግሞ በሶስት ቀናት ውስጥ ይፈፀማል።

- ኢየሱስ ክርስቶስ በተናገረው ታሪክ ውስጥ አስሩ ልጃገረዶች የሙሽራውን መምጣት እየተጠባበቁ ነበር። ምናልባትም ሙሽራው ሙሽራይቱን ይዞ በሚሚጣበት አዳራሽ ውስጥ ሳይሆኑ አይቀሩም። ሰዓቱ ምሽት ስለነበርም ሁሉም ኩራዝ ይዘዋል።

- ብዙ ጠበቁ። ነገር ግን የሰርጉ ሥርዓት ገና አልጀመረም። እየመሸ ሲሄድም እንቅልፍ እንቅልፍ አላቸው። ቀስ በቀስም ሁሉንም እንቅልፍ ይዟቸው ሄደ።

- አንድ ሰውም፣ “ሙሽራው መጣ፤ ወጥታችሁ ተቀበሉት፣" አለ። ሁሉም ከመኝታቸው ተነሱ። ሆኖም አንዳንደቹ ኩራዞች መጥፋት ጀምረው ነበር።

- አምስቱ ብልህ ልጃገረዶች ቀደም ብለው ለእንደዚህ አይነቱ ችግር ራሳቸውን አዘጋጅተው ነበር። ሙሽራው ቢዘገይ እንኳን ብለው ኩራዛቸው ውስጥ የሚጨምሩት ትርፍ ዘይት ይዘው ነበር።
- አምስቱ ሰነፍ ልጃገረዶች ግን ትርፍ ዘይት አልያዙም ነበር። ከብልሆቹ ልጃገረዶች ጥቂት ዘይት መዋስ ፈለጉ። ነገር ግን ብልሆቹ ልጃገረዶች ለማዋስ ፈቃደኞች አልነበሩም። ምናልባት ለእኛስ ቢያንስብን ብለው ስለፈሩ ዘይት አላዋሷቸውም። ስለዚህ በጊዜ ዘይት ወደሚሸጥበት ቦታ ሄደው ዘይት ገዝተው እንዲመጡ መከሯቸው። ስለዚህ ዘይት የሚሸጥ ነጋዴ ፍለጋ ሄዱ።

- እነርሱ በሄዱበት ወቅትም ሙሽራው መጣ። ከዚያም እርሱን ሲጠባበቁ የነበሩት አምስቱ ብልህ ልጃገረዶችና ሌሎቹ የሰርግ ታዳሚዎች ከሙሽራው ጋር ወደ አዳራሹ ገቡ። የአዳራሹ በርም ተዘጋ።

- ይህ ከሆነ በኋላ አምስቱ ሰነፍ ልጃገረዶች መጡ። በሩ እንዲከፈትላቸው ተጣሩ። በአሳዛኝ መልኩም ሊገቡ የሚችሉበት ምንም አይነት መንገድ አልነበረም። ሙሽራውም እንዲህ ብሎ መለሰላቸው፣ “እውነት እላችኋለሁ አላውቃችሁም።”

- የዚህ ምሳሌ ዋነኛ መልእክትን በተመለከተ ብዙ ሀሳቦች አሉ። አንድ ሀሳብ ግን ጎልቶ ይታያል። በአኗኗራችን ሁሉ ለኢየሱስ ዳግመኛ መመለስ ዝግጁ ሆነን መጠበቅና መዘናጋት እንደሌለብን ነው።

*የብልሆቹና የሰነፎቹ ልጃገረዶች ታሪክ የሚገኘው በማቴዎስ ወንጌል በምዕራፍ 25፡ 1 – 13 ባለው ክፍል ውስጥ ነው።*